የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ - ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 48
ADDIS ABABA-26th Jan., 20007

ማውጫ

በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ፫ሺ፯፻፳ ገጽ

CONTENTS

Council Of Ministers Regulations To Provide For The Obligatory Use Of Sales Register Machines 3720 Page

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፱/፲፱፻፺፱

በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፷፬ እና በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፩፻፲፯ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል ።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ስለ መጠቀም ግዴታ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፱/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፣

፩. ‹‹ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ›› ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ነው ፣

፪. ‹‹የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ›› ማለት በሽያጭ መደበኛ ደረሰኝ ፋንታ የሸቀጦችን ወይም የአገልግሎቶችን ሽያጭ የሚመዘግብና ለማንበብ ብቻ የሚቻል ማስታወሻን የሚያከማች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ፕሮግራም የሚደረግ ቺፕ የተገጠመበት በሰርክዩት የተጋገረ ፕሮግራም የሚጠቀም መሣሪያ ነው ፤

Council of Ministers Regulations No. 139/2007

COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE OBLIGATORY USE OF SALES REGISTER MACHINES

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005, Article 64 of the Value Added Tax Proclamation No. 285/2002 and Article 117 of the Income Tax Proclamation No. 286/2002.

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

These Regulations may be cited as the "Obligatory Use of Sales Register Machines Council of Ministers Regulations No. 139/2007".

2. Definitions

In these Regulations unless the context requires otherwise:

1) "Sales Register Machine" means a cash register machine or a point-of-sale machine:

2) "Cash Register Machine " means a machine that uses a Firm Ware that is installed in an electronic programmable read only memory chip and can record the sale of goods or services, in lieu of the regular sales receipt;

፫. «ደረሰኝ» ማለት የጥሬ ገንዘብ ሽያጭ ደረሰኝ ሲሆን ፤ የዱቤ ሽያጭ ኢንቮይስንና ያለክፍያ የሚሰጥ የዕቃ ወይም የአገልግሎት ማስተላለፊያ ደረሰኝን ይጨምራል ፤

፬. «በሰርክዩት የተጋገረ ፕሮግራም» ማለት በማይቀያየር ማስታወሻ ላይ የሚጫን በትክክል ተለይቶ የተቀመጠን ሥራ ለማደራጀት እንዲያገለግል የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው ፤

፭. «የማይቀያየር ማስታወሻ» ማለት ኃይል ቢቋረጥም ተይዞ የቆየው መረጃ ተጠብቆ የሚቆይበት ማስታወሻ ነው ፤

፮. «የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ» ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያን የሚተካ ኮምፒውተራይዝድ የሆነ መሣሪያ ሲሆን፣ የደንበኞችን ትዕዛዝ ፣ የትዕዛዙን አፈፃፀም ሂደትና የዴቢትና የክሬዲት ካርድ ሂሣብን የመመዝገብና የመከታተል፣ በክምችት ያለን ዕቃ የመቆጣጠርና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ተጨማሪ አቅም ያለው መሣሪያ ነው ፤

፯. «ታክስ» ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስንና የገቢ ግብርን ያጠቃልላል ፤

፰. «ሚኒስቴር» እና «ሚኒስትር» ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገቢዎች ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

፱. «ባለሥልጣን» ማለት የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ነው ፤

፲. «የታክስ ባለሥልጣን» ማለት ባለሥልጣኑ ወይም በባለሥልጣኑ የሥልጣን ውክልና የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ነው ፤

፲፩. «አቅራቢ» ማለት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ለታክስ ከፋዮች በሽያጭ የሚያቀርብ ሰው ነው ፤

፲፪. «ሰው» ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው ::

፲፫. «ፊሲካል ፕሪንተር» ማለት የፊሲካል ማስታወሻ ያለው ሆኖ በሥራ ላይ ያለውን የውስጥ መገናኛ በመጠቀም ብቻ በማናቸውም የአሠራር ፕሮግራም ሊያገለግል የሚችል ፕሪንተር ነው፤

ክፍል ሁለት
የግብር ከፋይ ግዴታዎች

፫. በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የመጠቀም ግዴታ

በሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ ዝርዝራቸው የሚወሰን ታክስ ከፋዮች በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ዕውቅና የተሰጣቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በመጠቀም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት የሽያጭ ደረሰኞችን አዘጋጅተው የማውጣት ግዴታ አለባቸው ::

፬. ደረሰኞች ሊይዟቸው የሚገቡ መረጃዎች

፩. በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የተዘጋጀ የሽያጭ ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

3) " Receipt" means cash sales receipt and include credit sales invoices and receipts for the transfer of goods and services delivered or rendered free of charge;

4) "Firm Ware" means a program which is burned on a Non-Volatile Memory and which is used for the organization of an exactly defined field of application;

5) 'Non-Volatile Memory' means a type of memory that retains its contents when power is turned off;

6) "Point-of-Sale Machine" means a machine that is a computerized replacement for the cash register machine and had additional capability to record and track customers' orders and debit-credit card accounts, to manage inventory and perform similar tasks;

7) "Tax" includes value added tax and Income Tax;

8) "Ministry" and "Minister" means the Ministry and Minster of Revenue, respectively;

9) "Authority" means the Federal Inland Revenue Authority;

10) "Tax Authority" means the Authority or tax office of a regional state or a city administration that is given delegated power by the Authority;

11) "Supplier" means a person who supplies sales register machines to taxpayers;

12) "Person" means a natural or a juridical person.

13) "Fiscal Printer" means a printer with a fiscal memory that can work with any application program using an existing interface, exclusively.

PART TWO
OBLIGATIONS OF TAXPAYERS

3. *Obligatory Use of Sales Register Machines*

Taxpa yers specified in directives to be issued by the Minster shall be subjected to the obligatory use of Sales Register Machines that are accredited in accordance with the provisions of these Regulations, to generate sales Receipts as provided for in Article 4 herein.

4. *Data Requirements of Receipts*

1. Any Sales Register Machine generated receipt shall indicate the following data:

ሀ) በታክስ ባለሥልጣኑና የንግድ ሥራ ፈቃድ በሰጠው አካል የተመዘገበውን የታክስ ከፋዩን ስም ፤

ለ) የንግዱን ስም፤

ሐ) የታክስ ከፋዩን መለያ ቁጥር፤

መ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ሥሪትና ሞዴል ዕውቅና ሰርቲፊኬት ቁጥር ፤

ሠ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን የምዝገባና የመጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር ፤

ረ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ጥቅም ላይ የዋለበትን አድራሻ ፤

ሰ) የደረሰኙን ቁጥር ፤

ሸ) ሽያጩ የተከናወነበት ቀን ፤

ቀ) የተሸጠውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ዓይነትና ብዛት ፤

በ) የሽያጩን ዋጋ ፤

ተ) ታክስ ከፋዩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተሰጠው ፈቃድ መሠረት ክፍያዎችን በውጭ ምንዛሪ በጥሬ ገንዘብ የሚቀበል ከሆነ ክፍያውን የተቀበለበትን የውጭ ምንዛሪ ዓይነት፣ ክፍያው በክሬዲት ወይም በዴቢት ካርድ የተፈፀመ ከሆነ የክሬዲት ወይም የዴቢት ካርዱን ያወጣውን ኩባንያ የንግድ ስም ፤

ቸ) ሚኒስቴሩ በሚያውጣው መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች መረጃዎች ፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(በ) መሠረት የሚጠቀሰው የሽያጭ ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸውንና የማይከፈልባቸውን ሽያጮች ጠቅላላ ድምር ለያይቶ ማሳየት አለበት ።

፫. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚጠቀም የንግድ ድርጅት ፣ ገዥው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ታክስ ከፋይ ካልሆነ በስተቀር ፣ በመሣሪያው ተዘጋጅቶ በሚወጣው ደረሰኝ ላይ የገዥውን ስም ፣ የንግድ ዓይነት ፣ አድራሻና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን የማሳየት ግዴታ የለበትም ፤ መሣሪያው እነዚህን መረጃዎች ለማሳየት የማይችል ከሆነም በታክስ ባለሥልጣኑ በተሰጠ ፈቃድ መሠረት የታተመ ደረሰኝ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ለሆኑ ገዥዎች የመስጠት ግዴታ ይኖርበታል ።

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከተው መሠረት በእጅ የተዘጋጀ ደረሰኝ በሚሰጥበት ጊዜ ሽያጩ በድጋሚ የሚመዘገብበት ሁኔታ እንዳይፈጠር በእጅ የተዘጋጀው ደረሰኝ ቅጂ በመሣሪያው ከተዘጋጀው ደረሰኝ ጋር ተያይዞ መቀመጥ አለበት ።

፭. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሁኔታዎች

፩. በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚጠቀም ታክስ ከፋይ ፤

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የሚሰጠውን በመሣሪያው ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ በቅድሚያ ማግኘት አለበት ፤

ለ) መሣሪያውን ጥቅም ላይ ሊያውል የሚችለው በመሣሪያው ለመጠቀም በሚያስችለው ፈቃድ ላይ ለተመለከተው የንግድ ሥራ ብቻ ነው ፤

a) The taxpayer's registered name with the Tax Authority and the licensing authority;

b) Name of the business;

c) The taxpayer's identification number;

d) Accreditation certificate number of the brand and model of the Sales Register Machine:

e) Registration and use permit number of the Sales Register Machine;

f) Address where the sales register machine is used;

g) The Receipt number

h) The date of transaction;

i) The type and quantity of goods or services sold;

j) Amount of the transaction;

k) If the taxpayers is authorized by the National Bank of Ethiopia to receive payments in foreign currency the receipt must show the type foreign currency received in cash or if payment is made by credit or debit card the trade name of debit or credit card issuing company;

l) Other information to be specified by directives issued by the Ministry.

2. The amount to be stated pursuant to Sub-Article 1(j) of this Article shall separately show the total taxable and non-taxable transaction values with respect to Value Added Tax.

3. A business enterprise using Sales Register Machine may not, unless the buyer is register for Value Added Tax, be obliged to show on the machine generated receipt the name, business type, address and tax payer's identification number of the buyer; and where the machine is not capable of showing such information, it shall have the obligation to issue receipts printed with the permission of the Tax Authority to buyers registered for Value Added Tax.

4. In the case of issuance of manually prepared receipt in accordance with Sub-Article (3) of this Article, the duplicate of such Receipt shall be attached to the machine generated receipt to avoid double counting of the transaction.

5. *Conditions for Using Sales Register Machines*

1. Any tax payer using a Sales Register Machine shall:

a) Obtain a use permit issued pursuant to Article 16 of these Regulations prior to the use of the machine:

b) Use the machine exclusively in the operation of the business covered by the permit;

ሐ) ለታክስ ባለሥልጣኑ አስቀድሞ በፅሑፍ ሳያስታውቅ የንግድ ስሙን መለወጥ ወይም በመሣሪያው ላይ የጥገና ፣ አቅም የማሳደግ ፣ ለውጥ የማድረግ ፣ የማሻሻል ወይም ወቅታዊ እንዲሆን የማድረግ ሥራ ማከናወን ወይም በማናቸውም ምክንያት ከቦታው ማንቀሳቀስ አይችልም ፤

መ) በመሣሪያው ላይ የጥገና ፣ አቅም የማሳደግ ፣ ለውጥ የማድረግ ፣ የማሻሻል ወይም ወቅታዊ እንዲሆን የማድረግ ሥራ ከተከናወነ በኋላ ይህንኑ ሥራ ካከናወነው ሰው ጋር በመሆን የተዘጋጀ መግለጫ ለታክስ ባለሥልጣኑ ያቀርባል ፤

ሠ) መናቸውንም የሂሣብ ሰነዶች የታክሱ ባለሥልጣን ታክሱን ለመወሰንና ለመሰብሰብ በሕግ እስከተፈቀደለት ጊዜ ድረስ ጠብቆ ማቆየት ይኖርበታል ፤

ረ) ማሣሪያውን በእርጅና ወይም በሽያጭ ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆን ለማድረግ በቅድሚያ ለታክስ ባለሥልጣኑ ማመልከትና ፈቃድ ማግኘት፣

ሰ) መሣሪያውን በመጠቀም የተከናወነውን የሽያጭ ተግባር የሚያሳይ መረጃ ለታክሱ ባለሥልጣን ማስተላለፍ የሚችል ተርሚናል በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ላይ መገጠም አለበት።

፪. ታክስ ከፋዩ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ በታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ በታተመ የሽያጭ ደረሰኝ ሊጠቀም ይችላል።

፫. የሚመለከተው የታክስ ባለሥልጣን ፤

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(መ) የቀረበለትን መግለጫ መነሻ በማድረግ መሣሪያው አገልግሎት ላይ ከመዋሉ በፊት መሣሪያውን መመርመርና መገምገም አለበት፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ረ) የተጠቀሰው ማመልከቻ ሲቀርብለት መሣሪያው አገልግሎት ላይ እስከነበረበት የመጨረሻ ቀን ድረስ የተመዘገቡ የሽያጭ መረጃዎች በተገቢው አኳኋን መያዛቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ምርመራ ማድረግ አለበት።

፬. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆን የሚሰጠው ፈቃድ መሣሪያው ከአገልግሎት ውጪ በሆነበት ቀን ፤

ሀ) የነበረውን የቆጣሪውን ንባብ ፤

ለ) የተከማቸውን አጠቃላይ ሽያጭ ድምር፣ እና

ሐ) በመጨረሻ ተዘጋጅቶ የወጣውን ደረሰኝ ቁጥር ማሳየት አለበት ።

፭. አግባብ ያለው የታክስ ባለሥልጣን በደረሰኝ ራስጌ ሊሰፍር የሚገባው ፅሑፍ እስከሚዘጋጅ ድረስ ታክስ ከፋዩ ከ፴ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ በሌላ ዓይነት ደረሰኝ እንዲጠቀም ካልፈቀደ በስተቀር ፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተዘረዘሩትን መረጃዎች ያልያዘ ለደንበኞች የሚሰጥ ደረሰኝ ለማዘጋጀት ተግባር እንዲውል ማድረግ አይቻልም ።

፮. ለደንበኞች በሚሰጠው ደረሰኝና ለኦዲት ጆርናል ሲባል በሚዘጋጀው ጥቅል ወረቀት ላይ የሚሰፍረው የግብይት ቁጥር ተከታታይነት ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ የቁጥር አሰጣጡ ሥርዓት ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ሰርኪዩት እንዲታወክ ወይም እንዲነካካ መደረግ የለበትም ።

c) Not, without prior written notice to the tax authority, change his business name or have the machine repaired, upgraded, altered, modified, updated or removed from its specified location;

d) Following the machine's repair, upgrade, alteration, modification or update and prior to its re-use, submit to the Tax Authority a joint statement prepared with the person who performed such works:

e) Preserved all accounting records for a period prescribed by law, within which the Tax Authority is authorized to make assesment and collection of taxes;

f) Apply to the Tax Authority and obtain its authorization prior to the withdrawal of the Sales Register Machine from use due to its wear and tear or sale.

g) Connect e-mobile to the Sales Register Machine which can transmit to the Tax Authority data of sales transactions carried out using the machine.

2. During the time when the Sales Register Machine is under repair, the taxpayer may use receipts printed with the approval of the tax authority.

3. The Tax Authority shall:
   a) Based on the statement submitted to it pursuant to sub-article 1(d) of this Article, inspect and evaluate the machine prior to its actual use;
   b) Upon receipt of the application referred to in sub-article 1(f) of this Article, undertake verification inspection to ensure that all sales data registered in the Sales Register machine up to the last day of its use are properly recorded.

4. The authorization for withdrawal of a Sales Register Machine from use shall indicate the following information as of the date of its withdrawal:
   a) The reading of the machine's counter;
   b) The accumulated grand total sales; and
   c) Number of the last receipt issued.

5. In no case shall a Sales Register Machine be used without the customer's receipt clearly indicating all the data required under the provisions of Article 4 of these Regulations unless the Tax Authority authorized such use, pending the completion of the installation of the official receipt header, for a period not exceeding thirty days from the date of the authorization.

6. In order to maintain the consecutive sequence of the transaction numbers imprinted on the customer's receipts and the audit journal tapes, the receipt numbering mechanism or circuit of a Sales Register Machine shall not be disturbed or tampered with.

. የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም ሁኔታዎች

በጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚጠቀም ታክስ ከፋይ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተደነገገውን ከማሟላት በተጨማሪ ፤

፩. ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ መሣሪያ ተፈላጊ ምቹን ረድፎች የያዘ በተገቢው አኳኋን የተ መዘገበ የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ የሽያጭ መዝገብ ሊኖረው ይገባል ፤

፪. በሁለቱም የጥቅል ወረቀቶች መጠቅለያ ወይም በተመሳሳይ አካላት ላይ የደረሰኝ ወረቀት ያልገባበት የሽያጭ ገቢ መመዝገቢያ መሣሪያ ጥቅም ላይ ማዋል የለበትም ፤

፫. ለደንበኛ በሚሰጠውና በኦዲት ጆርናል ደረሰኝ ወይም በተመሳሳይ ሰነዶች ላይ የሚታተመው ፅሑፍ ሊነበብ የሚችል እንዲሆንና በታክሱ ባለሥልጣን በሚወሰነው አኳኋን ተጠብቆ እንዲቆይ ማድረግ አለበት ፤

፬. የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ ንዑስ የሽያጭ መዝ ገብ ሁልጊዜም የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣ ሪያው በሚገኝበት ቦታ እንዲቀመጥና ሥልጣን የተሰጣቸው የታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኞች ለማመሳከር በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ እንዲያዩት ማድረግ አለበት ።

፯. የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ አጠቃቀም ሁኔታዎች

፩. የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያን የሚጠቀም ታክስ ከፋይ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተደነገገውን ከማሟላት በተጨማሪ ፣ እንዲጠቀምባቸው የተፈቀዱለት ሰነዶች ተከታታይ ቁጥር ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት በቀጣይ ጊዜያት የሚጠቀምባቸውን ሰነዶች ተከታታይ ቁጥር ከታክሱ ባሥልጣን ማስፈቀድ አለበት ።

፪. ማናቸውም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ የኤሌክ ትሮኒክ ጆርናል ሳይኖረው ሥራ ላይ ሊውል አይችልም ።

፫. የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ የሚጠቀም ታክስ ከፋይ ግብይቶችን በውጭ ምንዛሪ እንዲያከናውን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ከሆነ፣ በውጭ ምንዛሪ ያከናወናቸውን ግብይ ቶች የሚያሳይ መረጃዎችን በተጠየቀ ጊዜ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት ፤

፬. ማናቸውም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ፊስካል ፕሪንተር በመጠቀም ደረሰኝ ማውጣት አለበት ።

፰. የኮምፒዩተር መረጃ መረብ አጠቃቀም ሁኔታዎች

ማንኛውም ታክስ ከፋይ የንግድ ድርጅቱ የኮምፒዩተር መረጃ መረብን የሚጠቀም ከሆነ ፤

፩. የገዛውን ሶፍትዌር ዓይነት፣ የአምራች ኩባን ያውን ስም ፣ የፈቃድ ሁኔታ ፣ ለስንት ሽያጭ ነቁጣዎች እስከመቼ የሚያገለግል መሆኑንና የማደሻውን ወቅት ማስመዝገብ ፤

፪. ዳታቤዙ የሚስተናገድበትን ሰርቨር ሞዴል ፣ የሀርድ ዲስክ ቁጥርና የመረብ ካርድ ቁጥር ማስመዝገብ አለበት ።

6. *Condition for Using Cash Register Machines*

Any taxpayer using Cash Register Machines shall, in addition to the requirements of Article 5 of these Regulations:

1. maintain a duly registered Cash Register sales book showing the columns required for each machine used;
2. not use a Cash Register Machine without the corresponding tapes installed on both rollers or their equivalent;
3. ensure that the imprint on the customer's and audit journal tapes, or their equivalent is legible at all times and preserved as prescribed by the Tax Authority;
4. keep a subsidiary cash register sales book at all times at the place where the cash register machine is located, and make it available at any time for verification by duly authorized officers of the Tax Authority.

7. *Condition for Using Point-of-Sales Machines*

1. Any taxpayer using Point-of-Sales Machines shall, in addition to the requirements of Article 5 of these Regulations, obtain authorization from the Tax Authority for serial numbers to be used in the subsequent document range, at least one month before the previously authorized document range numbers are fully utilized.
2. No Point-of-Sale Machine shall be operated without the corresponding electric journal.
3. And taxpayer using point of sale machine shall, when requested, submit to the National Bank of Ethiopia reports which show transactions made in foreign currency in accordance with the authorization given by the National Bank of Ethiopia;
4. All Point of Sales Machines must use fiscal printers for issuing receipts;

8. *Conditions for Using Computerized Network*

Any tax payer shall, where its business firm uses a computerized network system:

1. cause the registration of the type of software purchased, the name of the manufacturing firm, the licensing conditions, number of Point-of-Sales and duration of use and renewal period;
2. cause the registration of the database terminal server model, hard disk number and network card numbers in the case of closed type software;

ክፍል ሦስት

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ተፈላጊ ባህሪያት

፱. የወል ባህሪያት

ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ፣

፩. የተመዘገበውን ቁጥር ማስተካከል በማይቻልበት አኳኋን ቢያንስ አሥራ ሁለት አኃዞች የሚደርስ የተከማቸ ጠቅላላ የሽያጭ መጠንን መያዝ የሚችል፣

፪. በተመዘገበው መረጃ ላይ ለውጥ ሲደረግበት፣ ወደሌሎች አሠራሮች ሊለወጥ ወይም የሽያጭ እንቅስቃሴዎች እንዳይመዘገቡ ለማድረግ በሚያስችል አኳኋን ሊቀየር የማይችል፣

፫. በየዕለቱ የተከናወነውን ጠቅላላ ሽያጭና የተከማቸውን ጠቅላላ ድምር የሚያሳይ ሪፖርት ማውጣት የሚያስችል፣

፬. የማይቀየር ማስታወሻ ያለው ወይም በውስጡ የተከማቸው መረጃ ቢጠፋ የጠፋውን መረጃ ማግኘት የሚያስችል ደጋፊ ሥርዓት ያለው፣

፭. የሽያጭ ዋጋ ቅናሽ፣ ተመላሽ ሂሣብና የመሳሰሉትን የሚያሳይና አከማችቶ ሊይዝ የሚችል፣

፮. የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸውንና የማይከፈልባቸውን የሽያጭ እንቅስቃሴዎች በግልጽ ለይቶ የሚያሳይና የእነዚህኑ የተጠቃለለ አጭር መግለጫ ማውጣት የሚያስችል፣

፯. የተከማቸውን መረጃ የታክስ ባለሥልጣኑ ታክሱን ለመወሰንና ለመሰብሰብ በሕግ እስከተፈቀደለት ጊዜ ድረስ ተጠብቆ እንዲቆይ ማድረግ የሚያስችል፣

፰. የኢንተርኔት ማስተላለፊያ ፕሮቶኮል ሶፍትዌር (ቲ.ሲ.ፒ./አይ.ፒ.) ማስተናገድ የሚችል፣

፱. ለታክስ ባለሥልጣን መ/ቤት የሽያጭ መረጃን ማስተላለፍ የሚችል የኢ-ሞባይል ቴክኖሎጂ መሣሪያ የተገጠመለት መሆን አለበት፣

፲. የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጨማሪ ባህሪያት

ማንኛውም የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ፣

፩. ለታክስ ኦዲት የሚያገለግል የኦዲት ጆርናል ጥቅል ወረቀት የሚይዝ መጠቅለያና ለእያንዳንዱ የሽያጭ ዓይነት የሚያገለግልና ተከታታይ ቁጥር ያለው ለደንበኛው የሚሰጥ የደረሰኝ ቅጂ የሚይዝ ሁለተኛ ጥቅል ወረቀት ማሽከርከር የሚችል ወይም ተመሳሳይ አቅም ያለው፣

፪. ከሁለቱ መጠቅለያዎች አንዱ ብቻ እንዲሰራ በተደረገበት ሁኔታ መሣሪያውን ማንቀሳቀስ እንዳይቻል የሚያደርግ የመቆጣጠሪያ ሥርዓት የተገጠመለት፣ እና

፫. የዋጋ ቅናሽና ተመላሽ ሂሣብ የመሳሰሉትን መረጃዎች ለደንበኛው በሚሰጠው ደረሰኝና በኦዲት ጆርናሉ ወይም ተመሳሳይ በሆነው ሰነድ ላይ ወዲያውኑ እንዲታተሙ የሚያደርግ፣ መሆን አለበት፣

፲፩. የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ተጨማሪ ባህርያት

ማንኛውም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ፣

፩. የተከናወነውን ማናቸውንም የሽያጭ እንቅስቃሴ ወዲያውኑና በተሟላ ሁኔታ መሣሪያው በተገናኘበት ሰርቨር ውስጥ መመዝገብ የሚችል፣

PART THREE

REQUIRED FEATURES OF SALES REGISTER MACHINES

9. *Common Features*

Any Sales Register Machine shall:

1. Have a non-convertible accumulating grand total sales with at least twelve digits;
2. Be tamper free, non-adjustable to other applications or free of other manipulations that will avoid the recording of sales transactions;
3. be capable of generating a report showing the reading of daily sales and the accumulated grand total recorded therein;
4. Have a non-volatile memory or be equipped with a recovery back-up system;
5. Reflect and store information such as sales discounts and refunds;
6. Be capable of clearly and separately indicating sales transactions that are subject to Value Added Tax and those which are non-taxable, and be capable of generating separate summary reports of same;
7. Be capable of preserving stored data for a period prescribed by law within which the Tax Authority is authorized to make assessment and collection of tax.
8. Support transmission control protocol (TCP/IP);
9. Be supported by e-mobile technology which can transmit sales data to the Tax Authority;

10. *Additional Features of Cash Register Machine*

Any Cash Register Machine shall, in Addition to the features described under Article 9 of these Regulations:

1. be equipped with a roller or its equivalent for the audit journal tape intended for tax audit purposes, and a second roller for the customer receipts tape the copies of which shall be consecutively numbered and issued for every sales transaction;
2. have a safety mechanism to prevent the operation of the machine in situations where only one of the rollers is used; and
3. be capable of printing, automatically, information such as sales discounts and refunds on the customer receipts tape and on the audit journal tape or its equivalent.

11. *Additional Features of Point-of-Sale Machines.*

Any Point-of-Sale Machine shall, in addition to the features described under Article 9 of these Regulations.

1. be capable of recording, automatically and completely, every sales transaction in the central server it is connected to;

፪. በታክስ ከፋዩ የሚቀርበውን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት የሚሰጥ የሽያጭ ደረሰኝ ማጠቃለያን የታክስ ባለሥልጣኑ ከመሣሪያው በማየት ትክክለኛነቱን ለማመሳከር የሚያስችል፣ እና

፫. የታክስ ባለሥልጣኑ የተሰረዙና የተከናወኑ ሽያጮችን ለመለየትና በታክስ ከፋዩ የሂሣብ መዝገብ ላይ ያልተመዘገቡ ሌሎች መረጃዎችን ማየት እንዲችል የመከታተያና የማረጋገጫ ዘዴዎች ያሉት፣

፬. ታክስ ከፋዩ ግብይቶችን በውጭ ምንዛሪ እንዲያከናውን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተፈቀደለት ከሆነ፣ በውጭ ምንዛሪ በጥሬ ገንዘብ የተቀበለውን የገንዘብ ዓይነት፣ ክፍያው በዴቢት ወይም በክሬዲት ካርድ የተፈፀመ ከሆነ፣ የክሬዲት ወይም የዴቢት ካርዱን ያወጣውን ኩባንያ የንግድ ስም ማሳየት የሚችል መሆን አለበት።

ክፍል አራት

ለሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ዕውቅና ስለመስጠትና ስለመመዝገብ

፲፪. ስለዕውቅና ማመልከቻ

፩. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አቅራቢ ማንኛውንም መሣሪያ ለሽያጭ ማቅረብ ከመጀመሩ በፊት የመሳሪያው ሥሪትና ሞዴል ዕውቅና እንዲያገኝ ለባለሥልጣኑ ማመልከት አለበት።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው ፎርም ላይ ተሞልቶ፣

ሀ) በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፱ እስከ ፲፩ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ተፈላጊ የሆኑትን የመሣሪያውን ባህሪያት ከሚያሳዩ ሰነዶች፣ እና

ለ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የአመልካቹን የንግድ ሁኔታ በሚመለከት ከሚጠየቁ አግባብ ካላቸው ሌሎች ሰነዶች ፣ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

፲፫. ማመልከቻዎችን ስለመመርመር

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ መሠረት የቀረበ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሥሪትና ሞዴል ዕውቅና ማመልከቻ ባለሥልጣኑ ባቋቋመው የዕውቅና ቦርድ ይመረመራል።

፪. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፱ እስከ ፲፩ የተዘረዘሩትን አግባብነት ያላቸውን ተፈላጊ ባህሪያት የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ አመልካቹ የመሣሪያውን ፍተሻና የፕሮግራሙን ሙከራ የቦርዱ አባላት በተገኙበት ማከናወን አለበት።

፫. ቦርዱ ማመልከቻውና ደጋፊ ሰነዶች ተሟልተው ከቀረቡለት ቀን አንስቶ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምርመራውን በማጠናቀቅ የውሳኔ ሀሳቡን ለሚመለከተው የባለሥልጣኑ ኃላፊ ማቅረብ አለበት።

፬. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰው የዕውቅና ቦርድ አባላት በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቅራቢነት በሚኒስትሩ ይሰየማሉ።

2. enable the tax authority to view from the machine and verify summaries, submitted by the taxpayer, of sales Receipts issued in accordance with Article 4 of these Regulations;

3. have monitoring controls and verification techniques to enable the Tax Authority to identify void sales and actual sales and other information not recorded in the taxpayer's accounts record.

4. if the Taxpayer is authorized by the National Bank of Ethiopia to receive payments in foreign currency, the machine must be capable of showing the type of foreign currency received in cash and if payment is made by debit or credit card be capable of indicating separately the trade name of debit or credit card issuing company;

PART FOUR

Accreditation and registration Of sales register machines

12. *Application for Accreditation*

1. Any supplier of sales Register Machines shall, prior to supplying any machine, apply to the authority for accreditation of the brand and model of the machine.

2. The application to be submitted in accordance with sub-article (1) of this Article shall be filled in a form issued by the Authority and be accompanied with:

   a) documents attesting the features of the sales Register machine as provided for in Articles 9 to 11 of these Regulations; and

   b) other appropriate documents relating to the status of the applicants business as may be required in accordance with directives to be issued by the Ministry.

13. *Examination of Applications*

1. An application submitted pursuant to Article 12 of these Regulations for accreditation of the brand and model of a sales Register Machine shall be examined by an accreditation board established by the Authority

2. The applicant shall conduct inspection of the Sales Register Machine and an actual system demonstration in the presence of members of the accreditation board to attest that the machine posses the relevant features specified under Article 9 to 11 of these Regulations.

3. The board shall complete its examination of an application for accreditation and submit its recommendation to the concerned officer of the Authority within five working days from the date it has received the duly presented application and supporting documents.

4. Members of the accreditation board referred to in this Article shall be appointed by the Minister upon the recommendation of the Director General of the Authority.

፲፬. የዕውቅና ሰርተፊኬት

፩. ባለሥልጣኑ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፱ እስከ ፲፩ የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ተፈላጊ ባህሪያት ማሟላቱ በዕውቅና ሰጭ ቦርድ ሲረጋገጥ ለመሳሪያው ስሪትና ሞዴል የዕውቅና ሰርቲፊኬት ይሰጣል፡፡

፪. ዕውቅና የተሰጣቸው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ስሪትና ሞዴል ዝርዝር በባለስልጣኑ ድረ ገጽ ይፋ መደረግ አለበት፡፡

፲፭. ዕውቅናን ስለመሰረዝ

ለሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ስሪትና ሞዴል የተሰጠ ዕውቅና ከሚከተሉት ምክንያቶች ባንዱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

፩. ዕውቅና የተሰጠው ሀሰተኛ ማስረጃ በመቅረቡ ሆኖ ከተገኘ፣

፪. ባለሥልጣኑ እንዲያውቀው ሳይደረግ በመሳሪያው ስሪትና ሞዴል ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ከተደረገ፣

፫. መሳሪያው በስራ ላይ ሲውል በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፱ እስከ ፲፩ የተዘረዘሩትን አግባብነት ያላቸውን ተፈላጊ ባህሪያት ሙሉ ለሙሉ አሟልቶ አለመገኘቱ ሲረጋገጥ፣ ወይም

፬. የዕውቅና ሰርቲፊኬት የተሰጠው ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ፣

፲፮. ምዝገባና የመጠቀሚያ ፈቃድ

፩. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አቅራቢ ለመሣሪያው ተጠቃሚ ሽያጭ ባከናወነ በ፭ ቀናት ጊዜ ውስጥ መሣሪያውን በሚመለከተው ታክስ ባለሥልጣን ዘንድ በተጠቃሚው ስም ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ለማስመዝገብ የሚቀርበው መረጃ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፣

ሀ) የተጠቃሚውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣

ለ) የተጠቃሚውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፣

ሐ) የመሳሪያውን ስሪት፣ ሞዴልና ተከታታይ ቁጥር፣

መ) የመሳሪያውን ቆጣሪ ንባብና ንባቡ የተካሄደበትን ቀን፡፡

፫. የታክስ ባለሥልጣኑ ምዝገባውን እንዳከናወነ በተጠቃሚው ስም የተዘጋጀ በመሣሪያው ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ መሣሪያውን ላስመዘገበው አቅራቢ ይሰጣል፡፡

፬. የመሣሪያው አቅራቢ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተሰጠውን ፈቃድ ለመሣሪያው ተጠቃሚ ያስረክባል፡፡

፭. ዕውቅና የተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በቀጥታ ወደ አገር ውስጥ ያስገባው ተጠቃሚው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከቱትን መረጃዎች ለባለሥልጣኑ አቅርቦ መሣሪያውን ማስመዝገብና በመሣሪያው ለመጠቀም የሚያስችለውን ፈቃድ ከባለሥልጣኑ መውሰድ አለበት፡፡

14. *Certificate of Accreditation*

1. The Authority shall issue certificate of accreditation with respect to the brand and model of a Sales Register Machine where the accreditation board ascertains that the machine possesses the relevant features specified under Articles 9 to 11 these Regulations.
2. A list of accredited brands and models of Sales Register Machines shall be posted at the Authority's website.

15. *Revocation of Accreditation*

An accreditation given with respect to the brand and model of any Sales Register Machine may be revoked where:

1. the accreditation was obtained by presenting false information;
2. any modification or upgrading is made to the machine without notifying the Authority;
3. the machine, in practice, fails to fully satisfy the relevant requirements stated under Articles 9 to 11 of these Regulations; or
4. the person holding the certificate of accreditation violates the provisions of these Regulations.

16. *Registration and Permit*

1. The supplier of a Sales Register Machine shall, within five days from the date of sales of the machine to any user, cause the registration of the machine by the concerned Tax Authority in the name of the user.
2. The information to be submitted for the registration of a sales register machines shall include the following:
   a) the taxpayer's identification number of the user;
   b) registration number of the user for value added tax;
   c) brand, model and serial number of the machine;
   d) the reading of the machine's counter and date of the reading.
3. The Tax Authority shall, upon registering the machine, provide the supplier with a permit issued in the name of the user authorizing the use of the machine.
4. The supplier shall handover the permit, issued pursuant to Sub-Article (3) of this Article, to the user of the machine.
5. Where the user directly imported the Sales Register Machine, it shall furnish the information referred to in Sub-Article (2) of this Article to the Authority and obtain a permit authorizing the use of the machine.

፮. በመሣሪያው ተጠቃሚ የሆነ ታክስ ከፋይ የተሰጠውን በመሣሪያው ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ ደንበኞቹ ሊያዩት በሚችሉት አኳኋን በመሳሪያው ላይ መለጠፍ አለበት፡፡ ማመሳከር እንዲቻልም የመሣሪያው ተከታታይ ቁጥር ጉልቶ በሚታይ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

፲፯. <u>የተሸጡ መሳሪያዎች ዝርዝር</u>

፩. የመሳሪያዎቹ አቅራቢ ለተጠቃሚዎች የሸጣቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ዝርዝር የያዘ መግለጫ እያንዳንዱ ወር በተጠናቀቀ በ፲፭ ቀናት ጊዜ ውስጥ ለሚመለከተው የታክስ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርበው መግለጫ ስለእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፣

ሀ) የመሣሪያውን ስሪትና ሞዴል፣
ለ) የመሣሪያውን ስሪትና ሞዴል ዕውቅና ሰርቲፊኬት ቁጥር፣
ሐ) የመሣሪያውን የምዝገባና የመጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፣
መ) የተሸጠበትን ቀን፣
ሠ) የምዝገባውን ቀን፣
ረ) የተጠቃሚውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፣
ሰ) መሣሪያው ጥቅም ላይ የሚውልበትን የንግድ ሥራ ዓይነትና አድራሻ፣
ሸ) የመሣሪያውን ቆጣሪ ንባብና ንባቡ የተወሰደበትን ቀን፣ እና
ቀ) የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያን በሚመለከት አገልግሎት ላይ የዋለውን ፕሮግራምና በፕሮግራሙ ላይ የተደረገውን ማስተካከያ፡፡

፫. የታክሱ ባለሥልጣን መግለጫው እንደደረሰው በራሱ ዘንድ ከሚገኘው የምዝገባ መረጃ ጋር ዝርዝሩን ማመሳከር አለበት፡፡

፲፰. <u>የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያን ለተለያዩ የንግድ ሥራዎች መጠቀምን ስለመፍቀድ</u>

፩. የታክሱ ባለሥልጣን የተለያዩ የንግድ ሥራ ዓይነቶችን የሽያጭ መረጃ ማከማቸት የሚያስችል አቅም ያለው የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ለተለያዩ የንግድ ሥራ ዓይነቶች የሽያጭ ደረሰኝ አዘጋጅቶ እንዲያወጣ ሊፈቅድ ይችላል፣ ሆኖም በተለያዩት የንግድ ሥራዎች የሚከናወነው ሽያጭ መሣሪያው በሚጠቀምበት ጥቅል ወረቀት ላይ በኮድ ወይም በምልክት ሳይሆን በቃላት በግልጽ ተለይቶ የሚጻፍ መሆን አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ፈቃድ እንዲሰጥ የሚቀርብ ማመልከቻ በመሣሪያው አቅራቢ ወይም ተጠቃሚ አማካይነት ለታክስ ባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት፡፡

6. A taxpayer who uses the machine shall affix the permit on the machine so that it shall be conspicuously visible to customers. The serial number affixed to the machine should also be printed in bold figures to facilitate verification.

17. *List of Machines Sold*

1. Any supplier of Sales Register Machines shall submit to the concerned Tax Authority, within fifteen days from the end of each month, a statement showing the list of machines sold to users.
2. The statement to be submitted pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall, with respect to each Sales Register Machine, contain the following information:
   (a) brand and model of the machine;
   (b) the accreditation certificate number of the brand and model of the machine;
   (c) the registration and use permit number of the machine;
   (d) the date of sale;
   (e) the date of registration;
   (f) the user's taxpayer identification number and registration number for Value Added Tax;
   (g) the type of business and the address where the machine is to be used;
   (h) the reading of the machine's counter and date of the reading; and
   (i) software used and customizations made thereto in case of a Point-of-Sales Machine.
3. Following submission of the statement, the Tax Authority shall reconcile the list with its own registration database.

18. *Authorizing the Use of Cash Registration Machine for Different Types of Businesses*

1. A Cash Register Machine with a built-in-capacity to accumulate sales data of different lines of business may be authorized by the Tax Authority to be used for issuing sales receipts for different lines of business; provided, however, that the distinction of sales by lines of business shall be clearly indicated on the machine tapes in words rather than in codes or symbols.
2. The application for obtaining the authorization referred to in Sub-Article (1) of this Article shall be submitted to the tax authority through the supplier or user of the machine.

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፱. ከታክስና ቀረጥ ነፃ ስለመሆን

ታክስ ከፋዮች እንዲጠቀሙባቸው ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ዕውቅና የተሰጣቸው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በገቢ ዕቃዎች ላይ ከሚጠየቅ ማናቸውም ታክስና ቀረጥ ነፃ ሆነው ይገባሉ፡

፳. ቅጣት

ይህን ደንብ በመተላለፍ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሳይጠቀም የተገኘ ወይም በመሣሪያው ተጠቅሞ የማጭበርበር ተግባር የፈፀመ ታክስ ከፋይ አግባብ ባለው የታክስ ሕግ በተደነገገው መሠረት በወንጀል ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የንግድ ፈቃዱ እንዲሠረዝ ይደረጋል፡፡

፳፩. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ታክስ ከፋዮች፣ ይህ ደንብ ከፀና በኋላ ዕውቅና የተሰጣቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ከገበያ ለማግኘት የሚያስፈልገውን ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚኒስቴሩ ለሚወሰን የመሸጋገሪያ ጊዜ፣ በታክሱ ባለሥልጣን ዘንድ ባስመዘገቡት የሽያጭ ደረሰኝ መጠቀም ይችላሉ፡፡

፳፪. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ሚኒስትሩ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳፫. ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን

የታክስ ባለሥልጣኑ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች በታክስ ከፋዮች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፳፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

PART FIVE
Miscellaneous Provisions

19. *Exemptions From Taxes and Duties*

Accredited Sales Register Machines, intended for use by taxpayers shall be exempted from import taxes and duties.

20. *Penalties*

Where a taxpayer, in violation of these Regulations fails to use Sales Register Machines or commits fraud using such machines, in addition to being held criminally responsible as provided by the relevant tax law, his business license shall be revoked.

21. *Transitory Provisions*

Taxpayers shall be allowed to use, after the effective date of these Regulations, sales receipts registered with the tax authority for a period to be determined by the Ministry in consideration of the time required to acquire accredited Sales Register Machines from the market.

22. *Power to issue Directives*

The Minister may issue directives necessary for the proper implementation of these Regulations.

23. *Power of Inspection*

The Tax Authority shall have the power to undertake inspection activities to ensure the observance of the provisions of these Regulations by Taxpayers.

24. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 17 day of August, 2007.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE